የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Science and Higher Education - Ethiopia

ቀን/Date: ጥር 30 2012
ቁጥር / Ref: ሣ2/ከ/ከ.ሬ/3536/12

ለአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ
ለአ/አበባሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርሲቲ
ለአዳማሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርሲቲ
ለሐረማያ ዩኒቨርሲቲ
ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ
ለባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ
ለአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ
ለዲላ ዩኒቨርሲቲ
ለጅማ ዩኒቨርሲቲ
ለመቐለ ዩኒቨርሲቲ
ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ
ለደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ
ለደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ
ለጅግጂጋ ዩኒቨርሲቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
ለሠመራ ዩኒቨርሲቲ
ለወሎ ዩኒቨርሲቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ
ለወለጋ ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርሲቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርሲቲ
ለወልዲያ ዩኒቨርሲቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርሲቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ
ለዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ
ለመቱ ዩኒቨርሲቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርሲቲ
ለኦዳቡልቱም ዩኒቨርሲቲ
ለራያ ዩኒቨርሲቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ
ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ
ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርሲቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርሲቲ
ለወራቤ ዩኒቨርሲቲ
ለጂንካ ዩኒቨርሲቲ
ለደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ
ለቀብሪደሃር ዩኒቨርሲቲ
ለኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ

**ጉዳዩ፡- የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀትን ይመለከታል!**

በዩኒቨርሲቲዎቻችን የሚገኙ ተማሪዎች ለበላቂ ጥቅማቸው መብታቸውን ለማስከበር በህግ በተፈቀደው መሠረት ተደራጅተው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የሚፈጠረውም የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀት ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ሰላማዊና በተልዕኮቻቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ጉልህ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ ስለሆነም ህብረቱ የተማሪዎችንና የሀገራችንን ብዝሃነት ማዕከል አድርጎ እንዲሁም የሴቶችን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ መልኩ ተደራጅቶ እንዲንቀሳቀስ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ይህ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት የአደረጃጀትና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ 003/2012 ተዘጋጅቷል፡፡

ስለዚህ ከታህሳስ 01/2012 ዓ.ም ጀምሮ በዩኒቨርሲቲዎች ያሉን የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀት ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር በተያያዘው 13 ገጽ የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀትና ምርጫ መመሪያ ቁጥር 003/2012 መሠረት እንዲሆን ተገቢው ሁሉ እንዲፈጸም እያሳወኩ ተግባራዊነቱ በመደበኛ ሪፖርት እንዲካተት አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሂሩት ወልደማርያም ተክለ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

**ግልባጭ፡-**

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለሚኒስትር ዴኤታዎች ጽ/ቤት (3)

ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር

www.moshe.gov.et info@ethernet.edu.et www.facebook.com/SHE.Ethio
☎ +251 11 8548738 ✉ :- 23976 CODE 1000

Scanned by CamScanner

# የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ህብረት

## አደረጃጀትና ምርጫ አፈጻጸም መመሪያ

ቁጥር-003/2012

አዲስ አበባ
ህዳር 2012 ዓ.ም

Scanned by CamScanner

**መግቢያ**

የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች በእውቀትና በክህሎት ዳብረው፣ መልካም ስነ-ምግባር ተላብሰው ብቁና ተወዳዳሪ፣ በራስ መተማመንን፣ ሐሳብን የመረዳትና የማስረዳት ብቃትን፣ ብስለትንና ምክንያታዊነትን ያዳበሩ ሆነው እንዲመረቁ ይጠበቃል። በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውም ከሙያ መስመራቸው በተጓዳኝ የአመራርነት ጥበብና ክህሎትን፣ በመተባበር፣ በመከባበር፣ በመተጋገዝ እና ሀገራዊ ራዕይ ያላቸው ሆነው ለራሳቸውና ለሌሎችም መብትና ግዴታዎች መጠባ አርዓያ መሆንን ተለማምደው እንዲመረቁ በተማሪዎች ህብረትና መሰል የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ መደላድል መፍጠር አስፈላጊ ነው።

ከሁሉ በላይ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሰላማዊ መማር ማስተማርን ለማረጋገጥና ለማስቀጠል ህብረቱ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚኖረውን ከፍተኛ ሚና በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ መጫወት እንዲችል የተሻለ ብቃትና ዝግጁነት ያለው ጠንካራ የተማሪዎች ህብረት እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ነው።

በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚኖር የተማሪዎች ህብረት አመራር በሚመረጥበት ወቅት እስካሁን የተስተዋሉ ክፍተቶችን በመሙላት ህብረቱን በማጠናከር የተሻለ ደረጃ ላይ በማድረስ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ህብረት ተቀራራቢ ደረጃ (ስታንዳርድ) እንዲኖራቸው በማስቻል ወጥ የሆነ የአመራር መምረጫ መስፈርት ማውጣት አስፈላጊ ነው።

የተማሪዎች ህብረት ምርጫ የሚከናወንበትና የሚመራበት ሀገራዊ መመሪያ ተሻሽሎ እንዲቀረጽ ከሚመለከታቸው አካላት በተለያዩ ጊዜያት ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እና የህብረቶቹ አሠራርና አመራር መርህን የተከተለ እንዲሆን ማስቻል ተገቢ ነው።

ስለሆነም የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀትና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ በሀገር አቀፍ የተማሪዎች ህብረት ቀርቦ በአባላቱ ሙሉ ፈቃድ ስምምነት ላይ ተደርሷል። የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርም ተቋማት ሊከተሏቸው የሚገባ የአሰራር ሥነ ሥርአትን ለማውጣት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 86 ንዑስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1፡- አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀትና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 003/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2፡- ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ መሰረት፡-

1. "መተዳደሪያ ደንብ" ማለት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ህብረት መተዳደሪያ ደንብ ነው።
2. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ህብረት ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ፓርላማ ነው።
3. "ዋና ሥራ አስፈፃሚ" ማለት በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ የህብረቱ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ዋና ፀሐፊ ነው።
4. "ሥራ አስፈፃሚ (ዘርፍ)" ማለት የተለያዩ የህብረቱን ዘርፎች በበላይነት የሚመራና ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ሹመቱ በዋና ሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቅ ነው።
5. "ተማሪዎች" ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም የሚማሩት ተማሪዎች ናቸው።
6. "የተማሪዎች ህብረት ወይም ህብረቱ" ማለት በተማሪዎች የተመረጠ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ህብረት ነው።
7. "ንኡሳን ኮሚቴ" ማለት እንደአስፈላጊነቱ የህብረቱን ሥራ ለማከናወን የሚቋቋምና በየዘርፉ አመራሮች የሚመሩ የተለያዩ ዘርፎች አባላትን የያዘ ነው። እነርሱም የጠቅላላ ጉባኤው አባላት የሆኑና በፍላጎት የተመረጡ እንዲሁም የየዘርፉን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያከናውኑ ናቸው።
8. "ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 መሠረት የተቋቋመ ማለት ነው።



Scanned by CamScanner

**አንቀጽ 3፡- ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ በተማሪዎች የተመረጡ፣ ሁሉንም ተማሪዎች የሚወክሉና ብቁ የህብረቱ አመራር በማስመረጥ የተደራጀና ጠንካራ የተማሪዎች ሕብረት በየዩኒቨርሲቲዎቹ እንዲቋቋም በማስቻል ሰላማዊ የመማር ማስተማር ለማረጋገጥና ለማስቀጠል ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑና የተጓዳኝ እውቀትና ክህሎት ባለቤት እንዲሆኑ ለመደገፍ የሚችል በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተቀራራቢ የሆነ ደረጃ (ስታንዳርድ) ያለው ጠንካራ የተማሪዎች ህብረት እንዲፈጠር ለማስቻል ነው።

**አንቀጽ 4፡- የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

**አንቀጽ 5፡- የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ባሉ ተማሪዎች ህብረት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## የአባላት መብቶችና ግዴታዎች

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 በአንቀጽ 38ና 39 እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የዲስፒሊን መመሪያ ቁጥር ሳከትሚ/002/2012 አንቀጽ 5ና 6 የተዘረዘሩት መብትና ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አባላት የሚከተሉት መብቶችና ግዴታዎች ይኖራቸዋል።

**አንቀጽ 6፡- የአባላት መብት**

1. ሁሉም አባል እኩል መብት አለው፤
2. የመምረጥና መመረጥና የህብረቱን እንቅስቃሴ አስመልክቶ ማንኛውንም መረጃ የመጠየቅና የማወቅ፤
3. በህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በቀጥታ ወይም በውክልና የመሳተፍ፤
4. ስለህብረቱ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት፤
5. በህብረቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ድምጽ የሚኖረው ሲሆን የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱም በህብረቱ ውስጠ ደንብ ይወሰናል።

**አንቀጽ 7፡- የአባላት ግዴታ**

1. ማንኛውንም የዩኒቨርሲቲውን ሕግና ደንብ የማክበርና የማስከበር
2. የህብረቱን መተዳደሪያ ደንብ፤ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን የማክበር፤
3. የህብረቱን አላማ የማክበርና በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ እንዲያገለግል ሲመረጥ የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት፤
4. በህብረቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት፤
5. የአባልነት መዋጮ በወቅቱ የመክፈል፤
6. ትምህርቱን ሲጨርስ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት ትምህርቱን ሲያቋርጥ ከህብረቱ የተሰጠውን መታወቂያና ለስራ የተረከበውን ንብረት የመመለስ እና
7. በህብረቱ ውስጥ ከአንድ የኃላፊነት ቦታ ወደ ሌላ የኃላፊነት ቦታ ሲሸጋገርና ከተለያዩ የሃላፊነት ደረጃዎች ሲወርድ በእጁ የነበሩ ንብረቶችን ለህብረቱ የማስረከብና የመውጫ ሪፖርት የማቅረብ

**አንቀጽ 8፡- የተከለከሉ ተግባራት**

1. ኃይማኖትን፣ የፖለቲካ አመለካከትን ወይም ብሔርን መሠረት ያደረገ ቅስቀሳ ማድረግ
2. በምርጫ ሰበብ ማንኛውንም ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶችን ማስተላለፍ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያልተፈቀዱ መልዕክቶችን የሚያስተላልፉ ቁሳቁሶችን፣ አልባሳትን፣ ጌጣጌጦችን፣ ባነሮችን፣ አርማዎችንና የተለያዩ ጽሑፎችን መጠቀም
3. ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደትን የሚያውኩ ተግባራትን መፈጸም




Scanned by CamScanner

## ክፍል ሶስት
## አደረጃጀት

**አንቀጽ 9፦ የህብረቱ መሠረታዊ አደረጃጀት**

1. ዩኒቨርሲቲዎች እንደነባራዊ ሁኔታቸውና እንደአስፈላጊነቱ በዋና ሥራ አስፈጻሚ ስር የሚደራጁ ዘርፎችን መጨመር ይችላሉ፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ህብረቱ የሚከተለው መሠረታዊ የአደረጃጀት መዋቅር ይኖረዋል፡፡






Scanned by CamScanner

**አንቀጽ 10፡- ጠቅላላ ጉባዔ (ፓርላማ)**

1. ጠቅላላ ጉባኤው የህብረቱ የበላይ አካል ነው፤
2. ጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ነው፤
3. ዋና ሥራ አስፈፃሚ (የህብረቱ ፕሬዚዳንት፣ ም/ፕሬዚዳንትና ዋና ጸሐፊ)፤ አፈ ጉባኤ፣ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰየሙ ይሆናል፡፡
4. ሥራ አስፈጻሚዎች ወይም የዘርፍ መሪዎች በሥራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በጠቅላላ ጉባኤው የሚጸድቁ ይሆናል፡፡ ተጠሪነታቸውም ለዋና ሥራ አስፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 11፡- ጠቅላላ ጉባኤ አወቃቀር**

1. ጠቅላላ ጉባኤው አባላት ብዛት በተቋሙ ውስጥ በሚገኘው የመማሪያ ክፍል ብዛት የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. በዩኒቨርሲቲው የትምህርት ክፍል ኃላፊ አስተባባሪነት ከተማሪዎች ህብረት ዋና ስራ አስፈጻሚ መሪነት ከእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ሁለት ተማሪ ተወካዮች (አንድ ሴትና አንድ ወንድ) በክፍሉ ተማሪዎች ተመርጠው የጠቅላላ ጉባዔው (ፓርላማው) አባል ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 12፡- የመማሪያ ክፍል ተወካዮች ሊያሟሉአቸው የሚገቡ መስፈርቶች**

1. መልካም ስነ-ምግባር ያላቸውና በተማሪዎች የሚታመንባቸው (ይህ ማለት በየትኛውም የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ያልተቀጣ)
2. የክፍሉ ተማሪዎች መብት ማስከበርና ግዴታቸውንም እንዲወጡ መደገፍ የሚችል
3. በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከትና በብሔር አድሎ የማያደርግ
4. በሁሉም የዩኒቨርሲቲው እና የህብረቱ ስብሰባዎች ላይ ለመገኘት የሚችልና ፈቃደኛ የሆነ
5. ኃላፊነቱንና ግዴታውን በአግባቡ አውቆ የሚወጣ
6. በህብረቱ የሚሰጡትን ስራዎች አሠራርንና መርህን ተከትሎ መስራት የሚችል
7. የአካዳሚክ ውጤቱ CGPA 2.75ና ከዚያ በላይ የሆነ

**አንቀጽ 13፡- የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር**

የህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ (ፓርላማ) የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ጠቅላላ ጉባኤው የህብረቱ የበላይ አካል ነው፤
2. አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ ያቋቁማል፡፡
3. አፈ-ጉባኤና የኦዲት ኮሚቴን ይመርጣል፤
4. ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን በአስመራጭ ኮሚቴ አስተባባሪነት ይመርጣል፡፡
5. በዋና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት (የዘርፍ መሪዎችን) እና የህብረቱን ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ ሹመትን ተወያይቶ ያጸድቃል፡፡
6. የህብረቱን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤ ያሻሽላል፤ ያጸድቃል፤
7. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤ ያሻሽላል፤ ያጸድቃል፤
8. በህብረቱ የሥራ ፕሮግራምና ስትራተጂ ላይ ውይይት አድርጎ ያጸድቃል፤ አቅጣጫ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
9. ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም በመመርመር ለቅድና በጀት ያፀድቃል
10. ዓመታዊ የሥራና የኦዲት ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፤
11. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በማዳመጥ ህብረቱ የተቋቋመበት ዓላማና የተነደፉ መርሃ ግብሮች ተግባራዊ መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጣል፤
12. የህብረቱ ሂሳብ በኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውጭ ኦዲተርም ይሰይማል፤
13. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እስከመሰረዝ ይወስናል፤
14. በህብረቱ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ህብረቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
15. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች ህጎች ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መመሪያ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 14፡- የጠቅላላ ጉባኤው ምልዓተ ጉባኤና ድምጽ አሰጣጥ፤**

1. በስብሰባው የተገኙ የፓርላማው አባላት ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
2. የጉባኤው ውሳኔዎች የሚተላለፉት በስብሰባው በተገኙ አባላት ከግማሽ በላይ ወይም በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡ ድምጽ እኩል ሲሆን አፈ-ጉባኤው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡



Scanned by CamScanner

3. የጠቅላላ ጉባኤው አባላት በማንኛውም ምክንያት ስንደሉ በዋና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስተባባሪነት ትምህርት ክፍል ኃላፊ ጋር በመሆን ከተጓደለበት መማሪያ ክፍል በምርጫ የሚተካ ይሆናል።

## ክፍል አራት
## የተማሪዎች ህብረት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ

**አንቀጽ 15፡-የምርጫ ሂደት**

የህብረቱ የምርጫ ሂደት ፓርላሜንተሪ የምርጫ ስርዓትን ይከተላል።

**አንቀጽ 16፡- አስመራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

1. አዲስ ዩኒቨርሲቲ ከሆነ በተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት ጠቅላላ ጉባኤው (ፓርላማው) አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን መርጦ ያቋቁማል።
2. ነባር ዩኒቨርሲቲ ከሆነ በነባር የተማሪዎች ህብረት አመራር አስተባባሪነት ጠቅላላ ጉባኤው (የመማሪያ ክፍል ተወካይ ተማሪዎች) ተሰብስቦ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ ያቋቁማል።
3. የአስመራጭ ኮሚቴ የሥራ ዘመኑ የአንድ ዙር ምርጫ ነው።

**አንቀጽ 17፡-የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት አሰያየም እና ዝርዝር አባላት**

1. ለነባር ተቋማት ከቀድሞ ህብረት አመራሮች ሶስት (3)፤
2. ከተማሪዎች ህብረት ሴቶች ጉዳይ ተጠሪ አንድ (1)
3. ለነባር ተቋማት ከፓርላማው ሶስት (3)፤ ለአዲስ ተቋማት የቀድሞ ህብረት አመራሮች ስለማይኖሩና ምርጫው ከፓርላማው ብቻ ስለምሆን ከፓርላማው ስድስት (6)
4. በአጠቃላይ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ብዛት ሰባት (7) ብቻ ይሆናል።

**አንቀጽ 18፡-አስመራጭ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ**

1. የምርጫ ኮሚቴ አባላት በፓርላማው አባላት በእጅ ጥቆማ ይመረጣሉ። ዕጩ ለመሆን 1/3ኛ ድጋፍ ማግኘት ይገባል።
2. የምርጫ ኮሚቴ አባላትን ለማስመረጥ በእጅ ጥቆማ ተወስዶ በፓርላማው አባላት የድጋፍና የተቃውሞ ድምጽ ይሰጣል።
3. በድምጹ ብዛት ቅደም ተከተል መሠረት የኮሚቴው አባላት ይሆናሉ።
4. የአስመራጭ ኮሚቴ አባል ለሕረብቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አመራርነት የመወዳደርና የመመረጥ መብት አለው። ነገር ግን ከተወዳደረ ከአስመራጭ ኮሚቴው ይወጣል። በተጠቋሚው ምትክ በድምፅ ብዛት ቅደም ተከተል መሠረት የመጀመሪያ የሆነው ይተከዋል።
5. የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ለሕረቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚነት የሚትወዳደር ከሆነ ምክትል የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ወይም ፀሐፊዋ የአስስራጭ ኮሚቴ አባል ትሆናለች።

**አንቀጽ 19፡- የአስመራጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

1. የኮሚቴውን ሰብሳቢ በስምምነት ይሰይማል።
2. የምርጫ ሂደቱ ከመጀመሩ ቀድሞ ለጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መመሪያ መሠረት የምርጫ መመዘኛዎችን፤ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስም ዝርዝርና አድራሻ እንዲሁም የቅሬታ አቀራረብ ሂደትን ለጉባኤው ያሳውቃል፤
3. የዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የአፈ-ጉባኤ እና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫ ያስፈፅማል።
4. እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ሂደቱ ላይ አሳስፈላጊ የምርጫ ቅስቀሳ ሲያደረግ በማስረጃ ከያዘ ወይም ከቀረበለት ተወዳዳሪውን ሙሉ በሙሉ ከምርጫው ሊያሰናብት ወይም እንደጥፋቱ መጠን ውጤት ሊቀንስ ይችላል። ይህንንም በግልጽ ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል።
5. የመወዳደሪያ የጽሑፍ ፈተናና ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችን ያዘጋጃል። እርሞ ውጤት ይሰጣል፣ ውጤቱንም ለሁሉም ግልጽ በሆነ መንገድ ያሳውቃል።
6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (5) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የዕጩ ተመራጮች ስትራቴጂክ ፕላን ግምገማን ግን ምስጥራዊነቱን ጠብቆና ከድ ስጥቶ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሉ በሚመለከታቸው አካላት እንዲታረምና ውጤት እንዲሰጥ ያደረጋል፤ ውጤቱንም ይይዛል፤ ከሌሎች ውጤቶች ጋር ያጠናቅራል።
7. በምርጫ ወቅት ድምጽ ይቆጥራል፤ የምርጫ ውጤትን ግልጽ በሆነ መንገድ ያሳውቃል።



Scanned by CamScanner

**አንቀጽ 20፦ የዋና ስራ አስፈጻሚ ዕጩ ተመራጮች ሊያሟሉአቸው የሚገቡ መስፈርቶች፦**

1. የዋና ሥራ አስፈጻሚ ዕጩ ተመራጭ የጠቅላላ ጉባኤው አባል መሆን አለበት።
2. በሚወዳደርበት ወቅት ያለው የትምህርት ውጤቱ CGPA 2.75 እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት።
3. መልካም ስነ-ምግባር ያለው ሊሆን ይገባል፤ በመሆኑም በማንኛውም በዲስፕሊን ጉዳይ ያልተቀጣ መሆን አለበት።
4. የተማረውን ጥቅም ከዩኒቨርሲቲው እና ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማመዛዘን ማስጠበቅ እንዲሁም የተማሪዎች መብት እንዲከበርና ግዴታቸውንም እንዲወጡ ማድረግ የሚችል
5. የተግባቦትና ራስን የመግለጽ ክህሎት ያለው እንዲሁም በራስ የመተማመን ችሎታ ያለው
6. በኃይማኖት፣ በብሔር፣ በፖለቲካ አመለካከት አድልዎ የማያደርግ ስለመሆኑ ቃል መግባት አለበት። የማይታይበት

**አንቀጽ 21፦ ዋና ስራ አስፈጻሚዎች ምርጫ አካሄድ**

1. ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚባሉት የህብረቱ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ዋና ፀሐፊ ናቸው።
2. የህብረቱ አስመራጭ ኮሚቴ ለዋና ስራ አስፈጻሚነት መወዳደር የሚፈልጉ የፓርላማው አባል የሆኑትን ተማሪዎችን በግልጽ ማስታወቂያ ይጠራል።
3. አስመራጭ ኮሚቴ ው መስፈርቱን ለሚያሟሉ አመልካቾች 40 ከመቶ ድምር ውጤት በሠርቲፊኬት፣ በጽሑፍ ፈተና፣ በቃለ መጠይቅ፣ በስትራጂክ ሰነድ ግምገማ በመስጠት ለይቶ ለፓርላማው ያቀርባል።
4. ፓርላማው ዕጩዎቹ በሚያቀርቡት ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት ምርጫ ያደርጋል። ይህም 60 ከመቶ የሚያዝ ይሆናል።
5. ዋና ሥራ አስፈጻሚው አጠቃላይ ድምር ውጤታቸው መሠረት የሚመረጡ ይሆናል።

**አንቀጽ 22፦ ዋና ስራ አስፈጻሚዎች ምልመላ ነጥብ አያያዝ**

1. ሠርቲፊኬት
   - 1.1. ከ5 ነጥብ የሚያዝ ይሆናል
   - 1.2. በበጎ ፈቃድ ወይም በበጎ አድራጎት ሥራዎች ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ባሉ ትምህርት ቤቶች ክበባትና ማህበራት ወይም የተማሪ አደረጃጀቶች ተሳትፎ ሠርቲፊኬቶችን ያካትታል፤
   - 1.3. ሶስት ሠርትፊኬትና ከዚያ በላይ ያመጡ ሙሉ አምስት ነጥብ የሚያገኙ ሲሆን ከዚያ በታች የሚያመጡት በአንጻራዊነት ተሰልቶ ነጥብ የሚያገኙ ይሆናል።
   - 1.4. ሠርቲፊኬቶቹ ከኦርጂናል ጋር የተጋናዘቡ ሊሆኑ ይገባል። ያልተገናዘበ ቅጂ ሰርቲፊኬት ብቻውን ዋጋ አይኖረውም።
   - 1.5. አመልካቾች ሠርቲፊኬት ከሌላቸው የተመደበው ነጥብ አይሰጣቸውም እንጂ ከውድድሩ አይታገዱም።

2. የጽሑፍ ፈተና
   - 2.1. የጽሁፍ ፈተና ከ10 ነጥብ የሚያዝ ይሆናል፤
   - 2.2. የጽሑፍ ፈተናው በአስመራጭ ኮሚቴ የሚዘጋጅ ሲሆን የፈተናዎቹ ይዘት እንደየዩኒቨርሲቲው ነባራዊ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል።
   - 2.3. የሚወጡት ፈተናዎች ሚስጥራዊ ሊሆኑና ለተወዳዳሪ ተማሪ በማንኛውም መንገድ ሊደርስ አይገባም። ይህ ሆኖ ከተገኘ እና አስመራጭ ኮሚቴው ተወያይቶ ካመነበት ፈተናው ውድቅ ይሆናል። ጥፋቱን ያጠፋም አባል ወይም ሌላ ተማሪ በዲስፕሊን ጥፋት ይጠየቃል። ስለሆነም ፈተናው የሚዘጋጀው ለፈተናው አንድ (1) ሠዓት ሲቀረው ይሆናል።
   - 2.4. የአስመራጭ ኮሚቴው ፈተና በሚፈትንበት ጊዜ የዩኒቨርሲቲው ተወካይ ሙሉ ሂደቱን ይከታተላል፤ ክፍተት እንዳለ ሲታመን ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ወዲያውኑ ሪፖርት ያደርጋል።
   - 2.5. ተፈታኞችም ይሁኑ አስፈታኞች በፈተና ዝግጅትና አሰጣጥ ላይ ምንም አይነት ስልክ ወይም የግንኙነት ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የተከለከለ ነው።

3. ቃለ መጠይቅ (ኢንተርቪው)
   - 3.1. ቃለ መጠይቅ ከ10 ፐርሰንት ይያዛል።
   - 3.2. የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች በአስመራጭ ኮሚቴው የሚዘጋጁ ይሆናሉ።
   - 3.3. ከላይ በ3.2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አስመራጭ ኮሚቴው በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሉ በሚመለከታቸው አካላት ጥያቄዎች እንድዘጋጁለት ማድረግ ይችላል።



Scanned by CamScanner

3.4. በጥያቄዎቹ መሠረት ሁሉም ተወዳዳሪዎች መልስ ሲሰጡ የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት እያንዳንዳቸው ውጤት ከአስር ነጥብ ይሰጣሉ። የተወዳዳሪው የቃለ መጠይቅ ውጤት የአስመራጭ ኮሚቴው አባላት የሰጡት ውጤት ድምር ለአባላቱ ብዛት ተካፍሎ የሚመጠው አማካይ ውጤት ሆኖ ይመዘገባል።

4. ስትራቴጂክ ዕቅድ

4.1. ስትራጂክ ዕቅድ ከ15 ነጥብ የሚያዝ ይሆናል።

4.2. ተወዳዳሪዎች ስትራቴጂክ ዕቅዳቸውን በሶፍት ኮፒ እና በሀርድ ኮፒ ለአስመራጭ ኮሚቴው በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ኮሚቴው ከሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ ዘግይቶ የሚቀርብ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም።

4.3. ከላይ (4.2) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ከባድ የሆነ የማህበራዊ ችግር መሆኑ ከታመነ ኮሚቴው ይህንኑ የሚገልጽ መረጃ በማያያዝ ሊቀበል ያስችላል።

**አንቀጽ 23፡- የመጨረሻዎቹን ስምንት እጩዎችን ስለመለየት**

1. አስመራጭ ኮሚቴ በጽሑፍ ፈተና ባስመዘገቡት ውጤት ቅደም ተከተል መሠረት የመጀመሪያዎቹን 16 አመልካቾች ለይቶ ለቃለ መጠይቅ ያቀርባል።
2. ለቃለ መጠይቁ የቀረቡ 16 ዕጩዎች ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ እንዲያቀርቡ ያደርጋል።
3. በሠርቲፊኬት (5 ነጥብ)፣ በጽሑፍ ፈተና(10 ነጥብ) ቃለ መጠየቅ (10 ነጥብ) እና በስትራቴጂክ እቅድ ግምገማ (15 ነጥብ) አጠቃላይ ድምር ውጤት (ከ40%) መሠረት የመጀመሪያዎቹ ስምንት (8) ተወዳዳሪዎች ስትራቴጂክ ዕቅዳቸውን ለጠቅላላ ጉባኤው እንዲያቀርቡ ያደርጋል።

**አንቀጽ 24፡-ህረቱን ህብረ-ብሔራዊ ማድረግና የሴቶች ተሳትፎን ማረጋገጥ**

1. ህብረቱን ህብረ-ብሔራዊ ማድረግ

1.1. ከላይ ባሉ አንቀጾች እንደተገለጸው የህብቱ አመራር ምርጫ በውድድር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋና ሥራ አስፈጻሚ ሳይም ይሁን የዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ ውስጥ የአንድ ብሔር ድርሻ ቢበዛ ሰላሳ ሶስት በመቶ (≤33%) ይሆናል።

1.2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1.1 የተገለጸውን ለማስፈጸም ከኮታው በላይ ተወዳዳሪዎች ከአንድ ብሔር አብላጫ ውጤት ያመጡ ከሆነ በውጤቱ ቅደም ተከተል መሠረት ቀጥሎ ያለው የሌላ ብሔር ተወዳዳሪ ይሰየማል።

1.3. የህብረቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ ህብረ ብሔራዊ መሆኑ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ይረጋገጣል።

1.4. በተመሳሳይ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ውስጥ የአንድ ብሔር ኮታ ቢበዛ ሰላሳ ሶስት በመቶ (≤33%) ይሆናል።

2. በህብረቱ አመራር ውስጥ የሴቶች ተሳትፎን ማረጋገጥ

የህብረቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ ውስጥ የሴቶች ኮታ ቢያንስ ሰላሳ ሶስት በመቶ (≥33%) ይሆናል።

**አንቀጽ 25፡- በፓርላማው የሚከናወን ምርጫና የዋና ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አሰያየም**

1. አጠቃላይ ሂደቱ በአስመራጭ ኮሚቴ ይመራል።
2. በምርጫ ወቅት የውጤት ልዩነቱን መሠረት ያደረገ አድልዎ እንዲፈጸም ዕድል ሊከፍት ስለሚችል ከ40% ያለውን የስምንቱን ዕጩዎች ድምር ውጤት ከምርጫ በፊት ለጠቅላላ ጉባኤው መግለጽ የተከለከለ ነው።
3. ተወዳዳሪዎች ያስገቡትን የመወዳደሪያ ስራቴጂክ ዕቅድ ለፓርላማው ቀድመው ባስገቡት ሰነድ መሠረት እኩል ሰዓት ተሰጥቶአቸው ያቀርባሉ።
4. ስትራቴጂክ ዕቅዱ ሲቀርብ ኃይማኖትን፣ የፖለቲካ አመለካከትን ወይም ብሔርን መሠረት ያደረገ ቅስቀሳ የተከለከለ ነው።
5. በማንኛውም ምክንያት አድሎ ማድረግ የተከለከለ ተግባር ነው።
6. ዕጩ ተመራጮቹ ሂደቱ ግልጽና ፍትሀዊ እንዲሆን የራሳቸውን አንድ ታዛቢ የማስቀመጥ መብት አላቸው።
7. አባላት ጥያቄዎቻቸውን እዚያው መድረክ ላይ ተወዳዳሪዎቹን እንዲጠይቁና ዕጩ ተመራጮች በዚያው መድረክ ላይ ምላሽ ወይም ማብራሪያ እንዲሰጡ ይደረጋል።
8. ፓርላማው ዕጩ ተመራጮቹን የሚመርጥበት ኮሮጆ በአስመራጭ ኮሚቴ ይዘጋጃል። ኮሮጆውም ታዛቢዎች በተገኙበት በፓርላማው ፊት ባዶ መሆኑ ተረጋግጦ ለምርጫ ዝግጁ ይደረጋል።



Scanned by CamScanner

9. ለፓርላማው አባላት የዕጩ ተመራጮችን ሙሉ ስም፤ ኮሌጅ/ፋኩልቲና የትምህርት ክፍል፤ የትምህርት ዓመትና ፎቶ የያዘ ወረቀት ለመራጭ የፓርላማው አባላት በመስጠት እንዲመርጡ ይደረጋል፤
10. የፓርላማው አባላት ለሁሉም ተወዳዳሪዎች (ለ8ቱ) ከስልሳ (ከ60%) ውጤት ይሰጣሉ። የአንዱ ተወዳዳሪ ውጤት አጠቃላይ በመራጮች የተሰጠ ውጤት ድምር ለአጠቃላይ መራጮች ተካፍሎ የሚመጠው አማካይ ይሆናል።
11. ምርጫው እንደተጠናቀቀ አስመራጭ ኮሚቴ የተወዳዳሪዎችን ውጤት ያጠናቅራል። ውጤቱንም ለሁሉም ግልጽ በሆነ መንገድ ያሳውቃል።
12. ዕጩ ተመራጮች በአጠቃላይ ውጤት ማለትም በአስመራጭ ኮሚቴው ከተሰጠው ከ40% ነጥብና በፓርላማው ከተሰጠው ከ60% ነጥብ ባመጡት ድምር ውጤት መሠረት ለዋና ስራ አስፈጻሚነት ይሰየማሉ። በዚሁ መሠረት ከ100% የመጀመሪያ ደረጃ ብልጫ ነጥብ ያመጣ ተመራጭ የህብረቱ ፕሬዚዳንት፤ ሁለተኛ ደረጃ ብልጫ ነጥብ ያመጣ የህብረቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ሶስተኛ ደረጃ ብልጫ ነጥብ ያመጣ የህብረቱ ዋና ጸሐፊ ሆኖ ይሰየማል።

13. የምርጫ ውጤት ስለመግለጽ
    - 13.1. የሶስቱ የዋና ስራ አስፈጻሚ አባላትን አጠቃላይ ውጤት፣ የተሰየሙበትን ኃላፊነትና ፎቶአቸውን የያዘ ማስታወቂያ በሁሉም የዩኒቨርሲቲው መግቢያ በሮች፣ ላይብራሪና ምግብ ቤቶችና እንዲሁም በሁሉም የዩኒቨርሲቲው የማስታወቂያ ሠሌዳዎች የሚለጠፍ ይሆናል። በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው ማህበራዊ ሚዲያዎችና በማህበረሰብ ሬዲዮ የሚገለጽ ይሆናል።
    - 13.2. በተመሳሳይ መልኩ አፈ-ጉባኤና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላትም ምርጫ ውጤት፣ የተሰየሙበት ኃላፊነትና ፎቶአቸው ይገለጻል።
14. የሹመት ደብዳቤ ስለመስጠት
    የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በምርጫ ውጤቱ መሠረት በአስመራጭ ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ ሲቀርብለት ለተመራጭ የሥራ አስፈጻሚዎች ኮሚቴ አባላት በሙሉ የሥራ ኃላፊነታቸውን በደብዳቤ ያሳውቃል።

**አንቀጽ 26፡-የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሪፖርት**

1. የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሁልጊዜ ያደረጋቸውን ስብሰባዎችና የሰጣቸውን ውጤቶችን ውዲያውኑ ማጠቃለያ ሠርቶ በአባላቱ የተፈረመ ቃለ-ጉባኤ (ቀን፣ ቦታ፣ ተሰብሳቢዎችንና የተሰጠውን ውሳኔ የያዘ) በጥንቃቄ ማስቀመጥ አለበት።
2. የሰርቲፊኬት ውጤት፣ የጽሑፍ ፈተና ውጤት፣ እያንዳንዱ አባል ለቃለ-መጠይቅ የሰጠው ውጤትና በዩኒቨርሲቲው በሚመለከተው ክፍል ስትራቴጅክ ዕቅድ ሰነድ ተገምግሞ የተሰጠ ውጤት የቅሬታ ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ በኮሚቴው በጥንቃቄ ሲያዝ ይገባል።
3. በመጨረሻም የማጠቃለያ ውጤት የያዘ ሪፖርት ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ግልባጭ ተደርጎ ለህብረቱ ዋና አፈ-ጉባኤ ይገባል።
4. በተጨማሪም ሌሎች በምርጫ ሂደት ላይ የተሰበሰቡ ዝርዝር ሰነዶችን፣ ማስረጃዎችንና ውጤቶችን የያዘ ሰነድ ለዋና አፈ-ጉባኤ ገቢ ይደረጋል። አፈ-ጉባኤውም የሥራ አስፈጻሚው ሥራ ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ያስቀምጣል።

**አንቀጽ 27፡- የዋና ሥራ አስፈጻሚ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ስራ አስፈጻሚው ለዋና ስራ አስፈጻሚነት ተወዳድረው በምርጫ ውድድር የቀሩትን ስራ አስፈጻሚ (የዘርፍ ኃላፊዎች) አድርጎ በዝንባሌያቸው፣ በልምዳቸውና በክህሎታቸው መሠረት መልምሎ ዕጩ ተሿሚ አድርጎ ለፓርላማው በማቅረብ ያስፀድቃል።
2. ዘርፎችን ያደራጃል፤ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ያወጣል፤
3. የተሾሙት ዘርፍ አመራሮች በስራቸው የሚሰሩ አባላትን፣ ንኡሳን ኮሚቴዎችን እና አጋዥ አካላትን እንዲመለምሉ፣ እንዲያደራጁ፤ እንዲያስተባብሩና እንዲመሩ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤
4. የዋና ሥራ አስፈጻሚ የሥራ ዘመን ሁለት አመት ነው። ጠቅላላ ጉባኤው ሲያምንበት ለአንድ ዙር በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል።

ክፍል አምስት
የአፈ-ጉባኤ እና የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ምርጫና አሰያየም

**አንቀጽ 28፡- አፈ-ጉባኤ**

1. አፈ-ጉባኤ ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች



Scanned by CamScanner

1.1. የጠቅላላ ጉባኤው አባል የሆነ
1.2. የሌሎችን ሐሳብ የመረዳት፣ ሐሳብን የመግለጽና የማስረዳት ክህሎት ያለው
1.3. በዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ
1.4. ውጤቱ CGPA 2.75ና ከዚያ በላይ የሆነ
1.5. ሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ ዓመት ተማሪ የሆነ

2. የአፈ-ጉባኤ ምልመላና አሰያየም
   2.1. አስመራጭ ኮሚቴ አፈ-ጉባኤ ለመሆን ለሚፈልጉ የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ለሰባት ቀናት የሚቆይ ለሁሉም ተማሪዎች በሚታዩ ቦታዎች የውድድር ማስታወቂያ ያወጣል።
   2.2. አስመራጭ ኮሚቴ ለተወዳዳሪ አመልካቾች ከ20% የሚያዝ የጽሑፍ ፈተና አውጥቶ ይፈትናል፣ እርሞም ውጤቱን ይይዛል።
   2.3. በጽሑፍ ፈተና ውጤቱ መሠረት የመጀመሪያዎቹን አምስት ተወዳዳሪዎች ለሚቀጥለው ቃለ መጠይቅ ውድድር ለይቶ ያሳውቃል።
   2.4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (2.3) መሠረት የተለዩትን አምስት ተወዳዳሪዎች ከ20% የሚያዝ የቃለ-መጠይቅ ፈተና አዘጋጅቶ እንዲፈተኑ ያደርጋል። የተወዳደረው የቃለ-መጠይቅ ውጤትም አስመራጭ ኮሚቴዎቹ የሰጡት አማካይ ውጤት ይሆናል።
   2.5. በጽሑፍ ፈተናና በቃለ መጠይቅ ፈተና ድምር ውጤት ሳይገለጽ በድምር ውጤት ቅደም ተከተል የመጀመሪያዎቹ ሶስት ተወዳዳሪዎች ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርበው እኩል ሰዓት ተሰጥቶአቸው በመረጡ ለህብረቱ የሚሰሩትን ሥራዎች በቃል ያቀርባሉ።
   2.6. ጠቅላላ ጉባኤውም ድምጽ ይሰጣል። በድምጽ ቆጠራው ከፍተኛውን ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ ከ60% ሙሉ ነጥብ ሲያገኝ ቀሪዎች ከዚያ አንጻር ይሰላሉ።
   2.7. በጽሑፍ ፈተና፣ በቃለ መጠይቅና በጠቅላላ ጉባኤው ድምጽ የተገኘው ውጤት በአንድ ላይ ተጠናቅሮ ከ100% ባለው ድምር ውጤት የመጀመሪያውን ከፍተኛ ውጤት ያመጣ ተወዳዳሪ ዋና አፈ-ጉባኤ እንዲሁም ሁለተኛውን ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ያመጣ ተወዳዳሪ ምክትል አፈ-ጉባኤ ሆኖ ይሰየማል።
   2.8. ተወዳዳሪዎች በማስታወቂያ የማይቀርቡ ከሆነ አስመራጭ ኮሚቴው ከፓርላማ አባላት መካከል መልምሎ ዋና አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈ-ጉባኤ ብሎ በዕጩነት ሰይሞ ለፓርላማው በማቅረብ ያስጸድቃል።

3. የአፈ-ጉባኤ ተጠሪነት
አፈ-ጉባኤ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።

4. የአፈ-ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር
   4.1. ጠቅላላ ጉባኤውን ይሰበስባል፣ ስብሰባ ይመራል።
   4.2. አፈ-ጉባኤው በስብሰባው ላይ የጉባኤው አባል የስነ-ምግባር ግድፈት ያሳየ እንደሆነ ከስብሰባው በጊዜያዊነት እንዲወጣ ማድረግ ይችላል።
   4.3. በሥራ አስፈጻሚ ወይም በ1/3ኛ የዘርፍ ሥራ አስፈጻሚዎች ወይም በ1/3ኛ የፓርላማው አባላት ጥያቄ ሲቀርብና ሲያምንበት አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ይችላል።
   4.4. የአፈ-ጉባኤን ዕቅድና ሪፖርት ለፓርላማው አቅርቦ ያስጸድቃል።
   4.5. ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሥራ አፈጻጸማቸውን ሪፖርት እንዲያቀርቡ ያደርጋል፣ በዚህም መነሻ የህብረቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለፓርላማው የተጠቃለለ ሪፖርት ያቀርባል።
   4.6. የአፈ-ጉባኤ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።
   4.7. በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**አንቀጽ 29፦ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ**

1. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ምልመላና አሰያየም
   1.1. የህብረቱ ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ዋና ኦዲተር፣ ምክትል ኦዲተርና ኦዲተር ዋና ሥራ አስፈጻሚ በተመረጠበት በዚያው ቀን በጠቅላላ ጉባኤው ለበቃው አምስት የፓርላማው አባላት በእጅ ተጠቁመው ድምጽ ከተሰጠ በኋላ በድምጽ ቆጠራ ውጤቱ መሠረት የመጀመሪያ ብልጫ ድምጽ የተሰጠው የፓርላማው አባል ዋና ኦዲተር፣ ሁለተኛው ምክትል ኦዲተር እና ሶስተኛው ኦዲተር ሆኖ ይሰየማል።
   1.2. የእያንዳንዳቸው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ህብረት ይወጣል።

2. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነት
የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል።



Scanned by CamScanner

3. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር
   3.1. የህብረቱ ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤
   3.2. የህብረቱ የሥራ እንቅስቃሴ መርሀን፣ አሠራርንና መመሪያን ተከትሎ መካሄዱን ያረጋግጣል፤
   3.3. ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፡፡
   3.4. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፡፡
   3.5. ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

**አንቀጽ 30፡- የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ምልመላና አሰያየም**

1. የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ምርጫና አሰያየም የህብረቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ምርጫና አሰያየም ሙሉውን ሂደት ተከትሎ ይፈጸማል፡፡
2. የሴቶች ጠቅላላ ጉባኤ ከየከፍሉ ከተመረጡ የህብረቱ አባል በሆኑ ሴቶች ይዋቀራል፡፡
3. የሴቶች ጠቅላላ ጉባኤ በተማሪዎች ህብረት ዋና ስራ አስፈጻሚ አስተባባሪነት የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡
4. በሴቶች ጉዳይ ጠቅላላ ጉባኤ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ዋና ጸሐፊ ሆነው ተመርጠው ይሰየማሉ፡፡
5. በሴቶች ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠችው የሴት ተማሪዎች ፕሬዚዳንት የተማሪዎች ህብረት የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ሆና ትሰየማለች፡፡
6. ተግባርና ኃላፊነታቸው በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ህብረት መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

**አንቀጽ 31፡- ልዩ ፍላጎት ዘርፍ ተጠሪ ምልመላና አሰያየም**

1. በዩኒቨርሲቲው ያሉ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አጠቃላይ ጉባኤ በህብረቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪነት የሚሰበሰብ ይሆናል፡፡
2. በልዩ ፍላጎት ጠቅላላ ጉባኤ በእጅ ጥቆማ ለስት ልዩ ፍላጎት ያለው ተማሪ ተጠቁሞ ለእያንዳንዳቸው ድምጽ ይሰጣል፡፡
3. በልዩ ፍላጎት ጠቅላላ ጉባኤ የመጀመሪያ ብልጫ ድምጽ በማግኘት የተመረጠው ተመራጭ የልዩ ፍላጎት ዘርፍ ተጠሪ ሆኖ ይሰየማል፡፡
4. ተግባርና ኃላፊነቱ በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ህብረት መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

**አንቀጽ 32፡-የቅሬታ አቀራረብ**

1. በምርጫ ሂደቱ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ምርጫው በተካሄደበት በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በጽሑፍ ያቀርባል፡፡
2. ቅሬታውም የተማሪዉን ሙሉ ስም፣ የትምህርት ክፍል፣ መማሪያ ክፍል፣ የቅሬታውን ዋና ጭብጥ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 33፡- ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ**

1. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም
   1.1. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
   1.2. አባላቱም ከዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት፣ መምህራንና ከነባር ተማሪዎች ይሆናል፡፡

2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪነት
   የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡

3. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር
   3.1. ከፕሬዚዳንቱ የተመራለትን ቅሬታ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሰውና የጽሑፍ መረጃ በማሰባሰብ የውሳኔ ሐሳብ የያዘና በአባላቱ የተፈረመ ቃለ ጉባኤ ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር በጽሑፍ ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፡፡
   3.2. ከማንኛውም አካል መረጃ የመሰብሰብ፣ አቅርቦ የመጠየቅ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 34፡- ይግባኝ ስለመጠየቅ**



Scanned by CamScanner

1. ቅሬታ አቅራቢው በፕሬዚዳንቱ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያልረካ እንደሆነ ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ ስብሳቢ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድም አጠርቶ በአንድ ሳምንት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጥ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## አባልነት የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

**አንቀጽ 35፡- የህብረቱ አባል አባልነቱ ሊቋረጥ የሚችለው፡-**

1. አባሉ በራሱ ፍቃድ ሲወስንና በጽሑፍ ሲጠይቅ፤
2. ከዩኒቨርሲቲው በማናቸውም ምክንያት ሲሰናበት ወይም ሲያቋርጥ፡፡
3. የህብረቱን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፤
4. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰናበት ሲወስን፡፡
5. ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ
6. ከላይ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የህብረቱ ጠቅላላ ጉባኤ በሚከተሉት ምክንያቶች አባል ከአባልነቱ እንዲታገድ ማድረግ ይችላል፤
    6.1. በዩኒቨርስቲው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የስነምግባር መመሪያ መሠረት (Code of conduct) አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ በሚያስቀጡ ጥፋቶች ላይ ተሳታፊ ሆኖ ከተገኘ፤
    6.2. በህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ ሲቀር፤
    6.3. ጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ምክር እና ተግሳጽ ባለማክበር ድጋሚ ጥፋት ሲያጠፋ
    6.4. ያለፈቃድና ያለበቂ ምክንያት ስብሰባዎችን ከሶስት ጊዜ በላይ የቀረና በዘርፍ ወይም በንዑሳን ኮሚቴዎች ውስጥ ቢያንስ በአንዱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አለማድረግ፤
    6.5. ጠቅላላ ጉባኤው አግባብ ነው ብሎ በሚያምነው በሌላ ምክንያት ከአባልነት ሊያሰናብተው ይችላል፡፡

**አንቀጽ 36፡- በስልጣን ሽግግሩ ወቅት የቀድሞው ህብረት ተግባርና ኃላፊነት**

1. የቀድሞው ህብረት አመራር አዲሱ አመራር ከተመረጠ በኋላ ከዩኒቨርሲቲው አመራር፤ ከሀገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ህብረት እና ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ጠቅላላ ስልጠና እና ኦሬንቴሽን የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል፡፡
2. የስልጣን ሽግግሩ ለተማሪዎች ግልጽ በሆነ መንገድ በማስታወቂያ፤ በማህበራዊ ድህረ-ገጽ እና በተለያየ መንገድ ሊተዋወቅ ይገባል፡፡
3. ቀድሞ ስሰራበት የነበረውን የህብረቱን የተሟላ ሀርድና ሶፍት ኮፒ ሰነዶችን ቆጥሮ ያስረክባል፡፡
4. የተደራጀ የመውጫ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለአዲሱ አመራር ከበቂ ማብራሪያ ጋር ያስረክባል፡፡
5. ከአዲሱ ሥራ አስፈጻሚና ከዩኒቨርሲቲው በተማሪዎች ህብርት ስላበረከተው አስተዋጽኦ የእውቅና ሠርቲፊኬት የመውሰድ መብት አላቸው፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 37፡- የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሥልጣን**

1. በህብረቱ ምርጫ ሂደት አላስፈላጊና ለግጭት የሚዳርግ ቅስቀሳ መኖሩን ሲያውቅ የምርጫ ሂደቱን በጊዜያዊነት ሊያስቆመው ይችላል፡፡
2. በምርጫ ኮሚቴ፤ በዕጩ ተወዳዳሪዎች፤ በፓርላማው አባላት ወይም በተማሪዎች በኩል ከምርጫው ጋር በተያያዘ የሚቀርቡትን ማንኛውንም ቅሬታዎች ወይም ጥቆማዎች እንደአስፈላጊነቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በማቋቋም አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡
3. ምርጫው ውጤታማ እንዲሆን የመተባበርና አስፈላጊውን ሁለንተናዊ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
4. ከምርጫው በኋላም አዲሱ ህብረት ፈጥኖ ወደ ሥራ እንዲገባና ጠንካራና ውጤታማ እንዲሆን የማስቻል ድጋፍ እንደአስፈላጊነቱ የመስጠት ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
5. የህብረቱ አመራር ህብረ-ብሔራዊ መሆኑንና የሴቶች ተሳትፎ ቢያንስ 20 በመቶ (፡20%) መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

**አንቀጽ 38፡-ከኃላፊነት ስለመታገድ**

1. ማንኛውም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የተሰጠውን ኃላፊነት ባለመወጣቱ ምክንያት የሥራ አስፈጻሚው በቃለ ጉባኤ አስደግፎ እንዲታገድለት ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሲያቀርብ ጠቅላላ ጉባኤው ተሰብስቦ እስኪወስን ድረስ በጊዜያዊነት ታግዶ ይቆያል፡፡



Scanned by CamScanner

2. የስራ አስፈጻሚ ሆኖ የተመረጠ አንድ አባል የዲስፕሊን ግድፈት ፈጽሞ የተከሰሰ እና በዚህም ከጽሑፍ ማስጠንቀቂ ጀምሮ ቅጣት የተወሰነበት ከሆነ በጊዜያዊነት የሥራ አስፈጻሚው የእግድ ውሳኔውን በቃለ ጉባኤ አስደግፎ ለፕሬዚዳንቱ በማቅረብ ያሳግዳል፡፡
3. በፍርድ ቤት በወንጀል ተከሶ የጥፋተኝነት ቅጣት የተፈረደበት እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ከሥራ አስፈጻሚ አባልነቱ ይሰናበታል፡፡

**አንቀጽ 39፡ሥራ አስፈጻሚ ሲጓደል ስለመተካት**

በማንኛውም ምክንያት የሥራ አስፈጻሚ አባል በቋሚነት ስጓደል ቀድመው ተወዳድረው በምርጫ ውጤታቸው ከተሸነፉት መካከል ሕብረ-ብሔራዊነትንና የሴቶችን ተሳትፎን በጠበቀ መልኩ በስራ አስፈጻሚ ተወስኖ በቃለ ጉባኤ ተደግፎ የተጓደለውን አባል እንዲተካው ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሲቀርብ ኃላፊነቱን የሚገልጽ የሹመት ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡ ጠቅላላው ጉባኤ ሲሰበሰብ ያጸድቃል፡፡

**አንቀጽ 40፡- ኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባል ስለመሆን**

የዋና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል (የዘርፍ አመራር) የሆነ ተማሪ በተጨማሪነት ወይም ደርቦ የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባል ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 41፡- በድጋሚ ስለመመረጥ**

የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ሲፈለግ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው እንደማንኛውም አዲስ ተወዳዳሪ ሙሉ ሂደቱን ተከትለው በተጨማሪነት አንድ የሥራ ዘመን ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 42፡- የተጠያቂነት ገደብ**

የተማሪዎች ህብረት ዋና ሥራ አስፈጻሚ የተማሪዎችን መብት ለማስከበር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሂደት በማንም ወይም በምንም ላይ ጉዳት እስካላደርሱ ድረስ ወይም በቅን ልቦና በሚያከናውኑት ተግባር ወይም በአጋጣሚ አደጋ በሚከሰት ነገር ወይም በልዩ ሁኔታ በተፈቀደ ተግባር በዲስፕሊን ጥፋት ሳይጠየቁ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 43፡- መመሪያውን ስለማሳወቅ**

1. የተማሪዎች ህብረትና የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር ይህንን መመሪያ ለሚመለከታቸው ሁሉ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት በዝርዝር የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ዩኒቨርሲቲው ይህ መመሪያ ለተማሪዎችና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት በተለያየ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 44፡- ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ በፊት ሲተገበሩ የነበሩ ከተማሪዎች ህብረት ምርጫ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎች በዚህ መመሪያ የተተኩ በመሆናቸው ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡ የተማሪዎች ህብረት ምርጫን የሚመለከቱ ሌሎች ህጎችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ መመሪያ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**አንቀጽ 45፡-የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት ሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማህበረሰብ አባላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 46፡- የህብረቱን መተዳደሪያ ደንብ የማውጣት ስልጣን**

በዩኒቨርሲቲ ያለው የተማሪዎች ህብረት ከዚህ "የተማሪዎች ህብረት አደረጃጀትና የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 003/2012" ጋር በትርጉምም ሆነ በአፈጻጸም የማይጋጭ ዝርዝር የህብረቱ መተዳደሪያ ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡



Scanned by CamScanner

**አንቀጽ 47፡- መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አጥጋቢ ምክንያቶች ሲኖሩ ወይም በሚመለከታቸው አካላት ጥያቄ ሲቀርብ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሊሻሻል ይችላል፡፡

**አንቀጽ 48፡- መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 01 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ፕሮፌሰር ሂሩት ወልደማሪያም

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር



Scanned by CamScanner